# ደንብ

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
(MCPS)

ተዛማጅ ሠነዶች፦ ABA, ABA-RB, ABC, ABC-RA, CNA, CNA-RA, COA-RB, EIB-RA, GCC-RA, GDA-RB, IPD-RA, JHC, JHC-RA

ኃላፊነት የሚመለከታቸው ዲቪዥኖች፦ Division of School Leadership and Improvement; Division of Human Resources and Talent Management

## በትምህርት ቤት የሚያገለግሉ በጎ-ፈቃደኞች

I. ዓላማ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ የወላጆች/የአሳዳጊዎች እና የማህበረሰብ በጎ ፈቃደኞችን አገልግሎት ለማበረታታት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የሚያስችሉ የአሠራር ሂደቶችን ማቋቋም።

II. ዳራ

የሁሉም ተማሪዎች አካደሚያዊ ጥረቶች እና ትምህርታዊ ተሞክሮዎች የሚዳብሩት እና የሚበለፅጉት ማህበረሰቡ በትምህርታቸው ላይ በሚሰጠው ትኩረት እና በሚያበረክተው አስተዋፅኦ ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ABC፣የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት ትብብር/አጋርነት፣ ጠንካራ የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት ግንኙነቶችን ለማበልፀግ እና የተማሪዎችን ስኬት ለማበረታታት በትምህርት ቤት ማህበረሰብ ውስጥ ባሉ ቤተሰቦች መካከል ጉልህ ግንኙነቶችን እና ማህበራዊ የግንኙነት መረቦችን የሚያዳብር የቤተሰብ ተሳትፎን ማጠናከር መሰረት ያደረገ አቀራረብ መበልፀግ እንዳለበት ይደነግጋል። በተማሪዎች የትምህርት ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ በጎ ፈቃደኞች የትምህርት ቤት ሰራተኞች የተማሪዎችን ፍላጎቶች በተሻለ ሁኔታ እንዲያሟሉ፣ ለተማሪዎች ተጨማሪ አርአያነትን እንዲያሳዩ እና የተማሪዎችን የትምህርት ተሞክሮ እንዲሁም ስለ MCPS የራሳቸውን ግንዛቤ እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል።

በጎ ፈቃደኞች ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ሌሎች የቤተሰብ አባላትን እንዲሁም በልጆች ትምህርት ላይ ፍላጎት ያላቸውን እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ተማሪዎችን ለመደገፍ ጊዜያቸውን እና ጉልበታቸውን ለመለገስ ፈቃደኛ የሆኑ ሌሎች የማህበረሰብ አባላትን ሊያካትቱ ይችላሉ።

III. የአፈጻፀም ሂደት

A. የትምህርት ቤት አመራር እና ማሻሻል ዲቪዥን (DSLI)/የተማሪዎች አመራር እና እንቅስቃሴ ክፍል የሚከተለው ኃላፊነት አለባቸው –

1. የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶችን እና ቢሮዎችን የወላጅ/አሳዳጊዎችን እና የማህበረሰብ በጎ ፈቃደኞችን አገልግሎት ለማበረታታት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም በሚያደርጉት ጥረት መደገፍ፣

2. የበጎ ፈቃደኞችን አስተዋፅኦ እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን በተመለከተ ለትምህርት ቤቶች ምርጥ ተሞክሮዎችን እና መመሪያዎችን ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች እና ለማህበረሰብ በጎ ፈቃደኞች ማሳወቅ፣ እና

3. የበጎ ፈቃደኝነት ፕሮግራም ልማት ላይ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት።

B. በጎ ፈቃደኞችን መመልመል፣ መመደብ፣ እና መተካትን በተመለከተ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት ያለው ርእሰ መምህሩ ነው። ለበጎ-ፈቃደኞች የሚፈቀዱ እንቅስቃሴዎች፣ በነዚህ ሳይወሰን፣ በመምህራን አመራር ተማሪዎችን ማገዝ፣ የመስክ ጉዞዎችን እንደ ሞግዚት ሆኖ መንከባከብ፣ እና የት/ቤት የማህበረሰብ ተሳትፎ ኩነቶችን መደገፍ የመሳሰሉትን ያካትታሉ።

C. ቦርዱ ወላጆች/አሳዳጊዎች በልጆቻቸው ትምህርት ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዳያደርጉ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ለመቀነስ ይፈልጋል። MCPS ወላጆች/አሳዳጊዎች በበጎ ፈቃደኝነት ተግባራት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዳያደርጉ እንቅፋት የሆኑ ማናቸውንም የአሠራር ስልቶችን ይመረምራል።

1. DSLI ከ MCPS የትምህርት ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር የገንዘብ እጥረትን ለመቀነስ አስፈላጊ ሪሶርሶችን መለየት አለበት፣ ለምሳሌ፡- ለአስፈላጊ የወንጀል ዳራ ማጣራት የጣት አሻራ ወጪን የመሳሰሉት ሁኔታዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች የጣት አሻራ ለሚያስፈልጋቸው ተግባራት በፈቃደኝነት እንዳይሰሩ እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ፣GCC-RB ደንብ፣የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች፣ MCPS እጩ ተቀጣሪዎች፣ ስለ ኮንትራክተሮች እና በጎ ፈቃደኞች የቀድሞ ታሪክ ምርመራ እንደተገለፀው።

2. DSLI ለዳራ ፍተሻ የጣት አሻራ መውሰድ የሚያስፈልጋቸው የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በተመለከተ አስፈላጊ ከሆነ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች ማሳወቅ እና

የጣት አሻራ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚችሉ የገንዘብ ምንጮች መኖራቸውን ማሳወቅ አለበት።

D. ርእሰ መምህራን/ተወካዮች የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሏቸው:-

1. ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ቤተሰቦች እና የማህበረሰብ አባላት መልካም አቀባበል የሚደረግላቸው እና በአክብሮት የሚስተናገዱበት አዎንታዊ አካባቢን በህንፃዎቻቸው ውስጥ ማመቻቸት።

2. ቢያንስ በየዓመቱ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች የበጎ ፈቃደኝነት እድሎችን እና ኃላፊነቶችን ማሳወቅ እና አስፈላጊ ከሆነም አቅጣጫ ማስያዝ እና ስልጠና መስጠት። ማስታወቂያዎቹ ለተወሰኑ ተግባራት የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የጣት አሻራ እና የወንጀል ዳራ ለማጣራት የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ስለ መሸፈን የገንዘብ ድጋፍ መኖሩን ጭምር መረጃ መስጠት አለባቸው።

3. የበጎ ፈቃደኞችን ተገቢ ክትትል ማድረግ አለባቸው።

4. ሰራተኞችን ከዚህ ደንብ እና ደንብ GCC-RB፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች፣ MCPS እጩ ተቀጣሪዎች፣ እጩ ኮንትራክተሮች፣ እና እጩ በጎ ፈቃደኞችን ስለ ዳራ የማጣራት ተግባር ማሳወቅ፣ ይህም በሜሪላንድ ህግ መሰረት "የህግ ጥሰት የፈፀሙ ጥፋተኞችን" ከበጎ ፈቃደኛነት አገልግሎት የሚያግድ ድንጋጌ ነው።

   a) የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር ዲቪዥን (DHRTM) የበጎ ፈቃደኞችን የበፊት ታሪክ ማጣራት እና የዩ.ኤስ የፌዴራል ምርመራ ቢሮ የእስር እና የክስ መዝገብ ፕሮግራም (RAPBACK) ቀጣይነት ባለው ክትትል ላይ በመመስረት፣ የበጎ ፈቃደኞችን ለበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ብቁነት በተመለከተ ለዋና ኃላፊዎች የማሳወቅ ሂደቶችን ይመሠርታል እና ይከታተላል፣ እና

   b) የበጎ ፈቃደኛን የበፊት ታሪክ ማጣራት እና RAPBACK መረጃ ሚስጥራዊ በመሆኑ፣ የተመደበ(ች)ው የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ጽሑፉን ለመቀበል የተፈቀደለ(ላ)ት ብቸኛው የትምህርት ቤት ሰራተኛ ነው። የበጎ ፈቃደኛው ለአገልግሎት ተስማሚ የመሆን ውሳኔ ለማይመለከታቸው የሥራ ባልደረቦች ወይም ለሌሎች በጎ ፈቃደኞች ሊጋራ አይችልም።

c) ርእሰ መምህራን ለበጎ ፈቃደኞች ስለሚያስፈልጉ የበፊት ታሪክ ማጣራት መስፈርቶች ማንኛውንም ጥያቄ ወይም ስጋት በመጀመሪያ DSLI ለአካባቢ ዳይሬክተራቸው ማቅረብ አለባቸው፣ እነሱም እንደ አስፈላጊነቱ DHRTM ካለው የበፊት ታሪክ ማጣራት ተቆጣጣሪ ጋር መማከር አለባቸው።

E. ሁሉም በጎ ፈቃደኞች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው:-

1. በጎ ፈቃደኞች በእያንዳንዱ የበጎ ፈቃድ እንቅስቃሴ መጀመሪያ እና መጨረሻ ላይ የጎብኚዎች አስተዳደር ስርዓት (VMS) በመጠቀም ወይም በሌላ መንገድ ወደ ሕንፃው መግባትና መውጣት እንዲሁም ሁልጊዜም የበጎ ፈቃደኛ መለያ ስም የተጻፈበት መለያ ማድረግ አለባቸው።

   a) VMS ሰራተኞች በአሜሪካ ስቴት ወይም ዲስትሪክት ኦቭ ኮሎምቢያ (ለምሳሌ:- የመንጃ ፈቃድ) የተሰጠ የጎብኚው(ዋ) ፎተግራፍ ያለው መታወቂያ እንዲቃኙ እና የጎብኚው(ዋ)ን መረጃ ከስቴት እና ከአካባቢው ከወሲብ ጥቃት ወንጀሎች ሪከርድ ጋር ማመሳከር ይችላሉ።

   b) ABA-RB ደንብ ላይ እንደተገለጸው፣ የትምህርት ቤት ጎብኚዎች፣ አንድ በጎ ፈቃደኛ በአሜሪካ ስቴት ወይም በዋሽንግተን ዲሲ የተሰጠ የፎቶ መታወቂያ ካርድ ማቅረብ ካልቻሉ፣ የትምህርት ቤቱ ሰራተኛ የግለሰቡ(ቧ)ን ስም በእጅ VMS kiosk ውስጥ ማስገባት እና ከዚያም የዩ.ኤስ የፍትህ መምሪያ ብሔራዊ የወሲብ ጥቃት ወንጀል መዝገብ ድረ ገጽ ላይ መፈለግ አለበት።

2. በጎ ፈቃደኞች የተማሪን ወይም የሰራተኛን ሚስጥራዊ ሪከርዶችን ማግኘት ወይም ተደራሽነት ሊኖራቸው አይችልም፣ እና የተማሪዎችን ሚስጥራዊነት መጠበቅ እና ማክበር አለባቸው።

3. ከተማሪዎች ጋር የሚሰሩ በጎ-ፈቃደኞች ሌሎች በሚያዩአቸው ሁኔታ መሆን አለበት (ለምሳሌ፣ መስኮት ወይም መዝጊያ ክፍት የሆነ ቦታ፣ ወይም ግልፅ በሆነ ህዝባዊ ቦታ መሆን አለበት)። በተወሰኑ ፕሮግራሞች፣ እንደ ማማከር የመሳሰሉ፣ በጎ-ፈቃደኞች ከአንድ ተማሪ ጋር አንድ-ለ-አንድ ለአጭር ጊዜ እንዲያሳልፉ ይጠየቁ ይሆናል። በጎ ፈቃደኞች አካላዊ ንክኪ ከማድረግ መቆጠብ አለባቸው፣ ወደተፈቀደላቸው ቦታዎች ብቻ መሄድ እና እንቅስቃሴዎችን ወይም የት እንዳሉ ለርእሰ መምህሩ ወይም ለሱፐርቫይዘሩ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።

4. በጎ ፈቃደኞች ተማሪዎችን መቅጣት የለባቸውም፣ ነገር ግን ስለ ተማሪዎች የባህሪ

ስጋቶችን ለሚቆጣጠረው ሰራተኛ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። በጎ ፈቃደኞች የተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ደህንነትን በተመለከተ ማንኛውንም ስጋት ለርእሰ መምህሩ ወይም ለሌላ ለሚመለከተው ሰራተኛ ማቅረብ አለባቸው።

5. በጎ ፈቃደኞች ሁሉንም የቦርድ ፖሊሲዎችን እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦችን እና መመሪያዎችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

6. በጎፈቃደኛን ያሳተፈ/ያካተተ ማናቸውም ዓይነት አደጋ/ጉዳት ወደ "MCPS Regulation EIB-RA፣ General Liability Insurance" ሪፖርት መደረግ አለበት።

**ተዛማጅ ሠነዶች፡-** Annotated Code of Maryland (MD Code), Education Article, §6-113, §6-113.1, and §6-113.2; MD Code, Criminal Law Article, §3-307, §3-308, §3-602, and §14-101; Code of Maryland Regulations 13A.15.02.07B (1)-(11)

**ስለ ደንቡ ታሪክ፡-** የቀድሞ ደንብ ቁ. 301-7፣ ፌብሩዋሪ 16, 1979፣ ዲሰምበር 1986 ተሻሽሏል፣ ኤፕሪል 5, 1994 ተሻሽሏል፣ ሜይ 5, 1999 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 14, 2014 ተሻሽሏል፣ ኦገስት 16, 2017 ተሻሽሏል፣ ዲሰምበር 16, 2025 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት  ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል" ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

በሜሪላንድ ስቴት የሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ት/ቤቶች በሙሉ የሚከተሉትን ህጎች በማክበር እንዲሠሩ የስቴቱ ፖሊሲ/ድንጋጌ ነው፡-

(1)የፌደራል ታይትል VI የዜኘት መብቶች ደንብ 1964፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-

- (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
- (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
- (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

የግንኙነት መርጃዎች እና የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይ የአካባቢ መስፈርቶች በተለያዩ ሕትመቶች መካከል ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል በዚህኛው ህትመት ላይ የተካተተው የሚፀና መሆኑን ልብ ይበሉ። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት እባክዎን ይህን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination.

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | MCPS ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ *** |
|---|---|
| Director of Student Conduct and Appeals<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator ሰክሽን 504 አስተባባሪ<br>Division of Specialized Support Services, Department of School Counseling<br>850 Hungerford Drive, Room 170, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | |
| Title IX Coordinator<br>Division of Equity and Organizational Development, Department of Student Conduct and Appeals<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ ማሳወቂያ የተሻሻለውን የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ ማሳወቂያ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር ይጣለጣል።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል። U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ  በአማራጭ ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ"Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች  የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ኦክቶበር 2025